# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ሰኔ ፱ ቀን ፪ ሺህ ፫ ዓ. ም
June 16, 2011

## ዛሬ በአንድነት ለመኖር መስማማት ካልቻልን፣ ነገ ሠላም፣ እኩልነት፣ አንድነትና ዴሞክራሲ በድንገት አይመጡም

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከተመሠረተበት ከ1964 ዓ.ም፣ በተለይም ደግሞ ለሕዝብ ይፋ ከወጣበት ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ መሬት ለአራሹ እንዲሆን፣ የዴሞክራሲያዊ መብት ያለገደብ እንዲበር፣ ለማኅበራዊ ፍትህ፤ ለብሄር/ብሄረሰቦች እኩልነትና የራሳቸውንም ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት፣ በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ አንድነትና ለሕዝባዊ መንግሥት መቋቋም ያደረጋቸው ተጋድሎዎች በታሪኩ ጎልተው የሚታዩ ናቸው። ለእነዚህ ሕዝባዊ ዓላማዎች መሳካትም ግምባሩን ሳያጥፍ በየጊዜው ሥልጣን ከያዙት አምባገነኖች ጋር ሲታገል ብዙ ሺህ አባላቱ ወደር የማይገኝለትንና ሲዘከር የሚኖር መስዋዕትነትን ከፍለው ማለፋቸውን ታሪኩን በቅንነት የተከታተለ ወገን ሁሉ ያውቀዋል።

ኢሕአፓ በአንድ በኩል ከኢትዮጵያ ምድር ማንኛውም ዓይነት ጭቆና ከሕዝባችን ጫንቃ ተሽቀንጥሮ ተጥሎ የዜጎች እኩልነት እንዲረጋገጥ አምርሮ ሲታገል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወገንን በጎጥ እያለያዩ፣ የእርስ-በርስ ጥላቻንና ቁርሾን በማራገብና ሕዝብን በማጋጨት የሀገርን አንድነት ስሜት ሲሸረሽሩ የቆዩትን ጠባብ ብሄርተኛ ቡድኖች ሳያሰልስ የፖለቲካ ዓላማዎቻቸውን ተቃውሟል፣ ታግሏቸዋል፣ በኃይል ሲመጡበትም ተዋግቷቸዋል።

በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ በሁሉም ብሄረሰቦች የጋራ መስዋዕትነት ከውጭ ወራሪ ጠላት እራሷን በመከላከል ዳር ድንበሯን አስጠብቃ የኖረችውን ሀገራችንን የተወሰኑ ክፍሎች ባዕድና ልዩ ሀገር አድርገው በማቅረብና ሀገራችንንም በቅኝ ገዢነት በመክሰስ፣ ሕዝቧንም በጠላትነት በመፈረጅ በሀገራችንና በሕዝቧ ጥቅም ላይ ሤራ የሚሸርቡ ቡድኖችንና ዓላማቸውን ድርጅታችን ሊቀበል ከቶም አይችልም። አንዳንዶቹ ፀረ-አንድነት ክፍሎችም ከዚህ መሰል ተግባር አልፈው ከውጭ ወራሪ ኃይል ጋር ወግነው፣ በወታደራዊ ባለሥልጣንነት ሳይቀር ተሰማርተው፣ ሀገራችንን ሲወጉ የነበሩ ከመሆናቸውም በላይ አሁንም ዕድሉ ቢመቻችላቸው ከተመሳሳይ ተግባር የማይመለሱ ናቸው። ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አልፋና ኦሜጋ በሕዝባዊ እኩልነትና ፍትህ ላይ የተመሠረተ የሀገሪቱ አንድነት በመሆኑ ይህን ዓይነት

850 Sligo Avenue Suite # 8
Siver Spring , MD 20910

P.O.Box 8141
Silver Spring, MD 20910

P.O.Box 88675
Los Angeles, CA 90009

Phone: 301-578-4466 Fax: 301-449-8363 Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com

ፀረ-አንድነትና አፍራሽ ተልዕኮ ተቀብሎና አስተናግዶም አያውቅም አሁንም አይቀበልም። ይህ የድርጅታችን አቋምም ከመጠን በላይ መስዋዕትነት የከፈልንበትና አሁንም አደባባይ ወጥተን በግልጽ የምንታገልለት አቋማችን እንጂ ከማናቸውም ወገን ይቅርታን የምንጠይቅበት ወይንም የምንሸማቀቅበት ጉዳይም አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም።

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደስብስብ በገዢው ቡድን በኩል ከሚደርስበት ጭቆናም ሆነ የመብት ረገጣ ለመላቀቅና በዜግነቱ የሚገባውን ሙሉ መብቱን ለማስከበር ትግል ማድረጉ የሚጠበቅ፣ አግባብ ያለውና ሊደገፍም የሚገባው መሆኑን ድርጅታችን ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አጥብቆ ያምናል። ከማመንም ባሻገር፣ ሀገራዊው ትግሉ መስመር እንዲይዝና እንዲሰምር፣ በብሄርም ሆነ በህብረ-ብሄር ደረጃ ተደራጅተው ትግል የጀመሩ ድርጅቶችን፣ የኢትዮጵያን ሀገራዊ አንድነት እስከተቀበሉ ድረስ፣ የአጠቃላዩ ሀገራዊ ትግሉ አካል አድርጎ ያያቸዋል። ከእነሱም ጋር ተባብረንና ሕዝባችንንም አስተባብረን ለግልጽ ዓላማዎች በመሥራት፣ በጫንቃችን ላይ ተጭኖ ያለውን የጭቆናና የግፍ አገዛዝ ለማስወገድና በምትኩም ሰላማዊና ሁሉን ያሳተፈ የሽግግር ሂደት ኖሮ አንድነቷ በተጠበቀላት ሀገራችን ውስጥ ወደ ቋሚ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ሥርዓት ሽግግር እንዲደረግም እንፈልጋለን። ይህን እውን ለማድረግም ድርጅታችን የመንግሥቱ ኃይለማርያም አምባገነናዊ መንግሥት ከመውደቁ በፊት ጀምሮ ዓላማውን የሚጋሩትን ኃይሎች የማሰባሰብ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) በኩል የተደረገው ትግል በዚህ ዙሪያ በምሳሌነት ይጠቀሳል።

ከሦስት አሥርተ-ዓመታት በላይ ያለሕዝባዊ ይሁንታ በነፍጣቸው ሥልጣን ላይ የወጡትን ሁለት ተከታታይ አምባገነን ገዢዎችን ለማስወገድ በተደረጉ የትብብር ጥሪዎችም ሁሉ ኢትዮጵያን በቅኝ ገዥነት ሲከሱ የነበሩትንና አሁንም እየከሰሱ ያሉትን ፀር-አንድነት ኃይሎች ሳይቀር፣ ኢትዮጵያዊነትን ተቀብለው ችግሮች የሚሏቸውን በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥና በኢትዮጵያዊ ሠፊ አጀንዳ ሥር ለመፍታት እንዲስማሙ ሲጠይቃቸው ነው ኢሕአፓ የኖረው። በሀገራችን ያሉትን ግፍና በደሎች፣ አድሎአዊነትንና መልከ-ብዙ ጭቆናዎችን ለማምከን እንዲቻል ለዴሞክራሲና ለፍትሃዊ ሥርዓት ምሥረታ የምናደርገውን ትግል እንዲቀላቀሉ ያላደረግነው ጥረትና ያልፈነቀልነው ድንጋይ የለም። ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ “የኢትዮጵያ ጉዳይ አያገባንም” በሚል ጥሪያችንን አንቀበልም ሲሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ለረጅም ጊዜ ውይይቱን ቀጥለውና የመስማማት ፍንጭም አሳይተው፣ ነገር ግን ብሄራዊ ትግሉ እንዲዘናጋና እንዲያዘግም በማድረግ በመጨረሻው ሰዓት እጥፍ ብሎ በመቅረት ጥረቱን ሁሉ ከንቱ ሲያደርጉ እንደኖሩ ሊነሳና ሊወሳ የሚገባው ሃቅ ነው። ያም ሁሉ ሆኖ ግን አሁንም ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ገዥ፣ ቢያንስ ከፊሉን ሕዝቧንም እንደ ጠላት ማየታቸውን እንደቀጠሉ ናቸው። አሁንም፤ በስሙ የሚናገሩለት ሕዝብ ተከተላቸውም አልተከተላቸው፤ በሕዝብ ስም የሚያስተጋቡትና የትግላቸውም ዋና ዓላማ አድርገው የሚያቀርቡት፣ ትናንት በሻእቢያና በህወሓት/ኢሕአዴግ ሤራ ከተቆረጠችው ኤርትራ በተጨማሪ፣ በምዕራቡ የሀገራችን ድንበር ለባዕድ ተቆርሶ ከተተሰጠውም የሀገራችን ክፍል በተጨማሪ፣ ለመቶ ዓመት ኪራይ በሚል ከሀገሪቱ ገበሬዎችና ከብት-

አርቢዎች እጅ ተፈልቅቆ እየተወሰደ ለባዕዳን ከሚቸበቸበው የተረፈውን ሀገራችንን መገነጣጠልና መቦጫጨቅ ነው።

ደርግ ለ17 ዓመቶች ሕዝቡን በግፍ ጨፍጭፎና የአንድነት ኃይሉንም አቅሙ የፈቀደለትን ያህል አዳክሞ፣ ሲያተራምስ ያቆያትን ሀገር ለህወሓት/ኢሕአዴግና ለሻእቢያ መሪዎች አስረክቦ ከተበተነ በኋላ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የማዳንና አንድነትዋንም እንደገና የመጠበቅ ከባድ ሃላፊነት በሀገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጫንቃ ላይ ወደቋል። ከአሁን በፊትም  የኢትዮጵያን ኀላዌና አንድነት ለመከላከል ነበር ኢዴኃቅ የተመሠረተው፣ ኢሕአፓም በምሥረታው ላይ ትልቅ ሚና የተጫወተው። ጉልህ ሀገርን የማዳን ሚና፣ ከሌሎቹ ሀገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጋር በአንድነት ለኢትዮጵያ ኅልውናና አንድነት የመቆም ሚና!!

ከኢዴኃቅ በኋላ ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ በተፈጠሩት በአማራጭ ኃይሎችና በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ሊካተቱ ከቻሉ የተለያዩ የብሄር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ድርጅታችን ሠርቷል፤ አሁንም እየሠራ ይገኛል። ከህብረ-ብሄር ድርጅቶች ባሻገር ድርጅታችን በጋራና በኅብረት ከጎናቸው ተሰልፎ አብሯቸው የሠራው የብሄር ድርጅቶች ከህብረ-ብሄር ድርጅቶች ጋር ከሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች ዋነኛው ሁሉም በኢትዮጵያዊነታቸው የማያወላዳ ዕምነት ያላቸው መሆናቸው ነው። እነዚህ የብሄር ድርጅቶች ለመብቱ እንታገልለታለን በሚሉት ብሄር/ብሄረሰብ ላይ ያለፉት ሥርዓቶች ያደርሱ የነበረውን በደልና ጭቆና እንዲሁም አሁን ያለው አገዛዝ፣ እያደረሰ ያለውን ግፍና በደል ለማስወገድ በቅድሚያ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማሸጋገር ያስፈልጋል የሚለውን ዕምነት የያዙ መሆናቸው ነበር ያስተሳሰረን። በሀገሪቱ ውስጥ አሁን ያሉትን የፍትህ ማጣትና የእኩልነት መብት መጓደል ከሚቀፈቅፋቸው አምባገነናዊ አገዛዝ ጋር ጨርሶ ለማስወገድ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ከዚህና ከዚያ ብሄረስብ ወይንም የዚህና የዚያ ዕምነት ተከታይ ነው በሚል ሳይከፋፈሉ በአንድ ላይ በመቆም መታገል አለባቸው ብለው ማመናቸው ነው አብረናቸው እንድንቆም ያደረገን። ባጭሩ፤ በእነዚህ ኅብረቶችና ቅንጅቶች የተሰባሰቡት ድርጅቶች የጋራ አቋም የብሄር ጭቆና ከሃገራዊ ፍትህና ርትዕ መጥፋት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ስለሆነ ይህንን ዓይነቱን ጭቆናም ሆነ ከዚህ የወጣውንና ሕዝብም በጋራ የሚጋራውን ማናቸውንም ዓይነት የመብት መገሠስ ለማሰወገድ ለጋራ ችግሮቻችን በጋራ ሀገራዊ መፍትሄ ማግኘት ይኖርብናል የሚል ነው።

ከላይ እንደገለጽነው ድርጅታችን ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በኢትዮጵያ አሉ የሚባሉ ፖለቲካዊ ችግሮች ሁሉ የዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎች ሀገራችን ውስጥ ሲፈጠሩ፤ የሰብዓዊ መብቶች ሲከበሩ፣ የፍትኅ መሠረት ሲጠናከር፣ የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ፣ ዛሬ የምናያቸው ውስብስብ ችግሮች ሁሉ መልክ ሊይዙና መፍትሄም ሊያገኙ ይችላሉ ብሎ ያምናል። ለዚህ ዓይነቱ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታም ካሁን በፊት ሲታገል እንደኖረው ሁሉ አሁንም ግምባሩን ሳያጥፍ ይታገላል። ፀረ-አንድነት ኃይሎች ይህንን አስተሳሰባችን ተጋርተውና ኢትዮጵያዊነትን ተቀብለው፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት አክብረው፣ በጋራ በዜጎች እኩልነት ላይ የተመሠረተች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት አብረውን

እንዲቆሙ እንፈልጋለን። ለዚህም ልንጎተጉታቸው፣ ልናበረታታቸው እንሻለን። ይህ ፍላጎታችን ብቻ አይደለም ዓላማችንም ነው።

በሥልጣን ላይ ያለው የፀረ-አንድነቱ ቡድን ቁንጮ እያደረ እንዳለው ሁሉ፤ እነዚህ ፀረ-አንድነት ኃይሎችም ቢሆኑ ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸው እነሱም በተራቸው  የሀገራችንን አንድነት ለመሰርሰርና ለመናድ ከመጣር አይቦዝኑም የሚለውን እምነታችንን ሊያስቀይረን የሚችል ሁኔታ እስካሁን አልተፈጠረም። ይህንን ስጋታችንን ሊያስወግዱ የሚችሉት ፀረ-አንድነት ኃይሎቹ እራሳቸው የያዙት አቋም ጊዜው ያለፈበት የቅኝ ገዥዎች መርዝ መሆኑን ተገንዝበው፣ እንወክለዋለን የሚሉት አብዛኛው ሕዝብም እምነታቸውን እንደማይጋራ ተረድተው፣ በዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ተስፋቸውን አድርገው፣ ከሕዝባቸው ጎን ለመቆም፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ አብረውን ለመታገል መወሰናቸውን በግልጽና በማያወላዳ መልክ ሲገልጹ ነው። ይህንንም በትክክል ለመግለጽ ሦስተኛ ድርጅት እንዲናገርላቸው፣ “ይህ ድርጅት አቋሙን ቀይሯል” ተብሎ በሌላ አፍ እንዲለፈፍላቸው የሚያስፈልጋቸው አይደለም። “ኢትዮጵያ ሀገራችን ናት” የሚለው እንዴት ይከብዳቸዋል? ይህንስ ማለት የሚሳነውን ቡድን እንዴትስ በኢትዮጵያ ጉዳይ ማመን ይቻላል? በተግባር ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ቆመው ሕዝብንና ሀገርን በጦር የወጉ ቡድኖች ጋር የመተባበር ጉዳይ ሲነሳስ ጥያቄ ማንሳታችን በምንስ መመዘኛ ሊያስከስን ይችላል? መተባበሩስ ለምንድን ነው? መተባበር እኮ እኔ የምፈልገውን እንዳገኝ እርዳኝ፣ አንተ የምትፈልገውን እንድታገኝ ደግሞ እኔ እረዳሃለሁ ማለት ነው። የሚፈልጉት ኢትዮጵያን መናድ እየሆነ እያለ፣ እንዴት ነው አንድ ኢትዮጵያዊና በኢትዮጵያ ላይ እምነት ያለው ድርጅት፣ ቡድንም ይሁን ግለሰብ የራሱን ማንነት የሚንደውን እንቅስቃሴ የሚተባበረው? “የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ” እንዲሉ እነዚህ ፀረ-አንድነት ኃይሎች እራሳቸው መልስ መስጠት ሲገባቸው የሌሎች ጥብቅና ለመቆም መሞከር ከኢትዮጵያ ጥቅም አኳያ ትርጉሙ ምን ሊሆን ይችላል።

ስለዚህም ነው፣ ህብረ-ብሄር ድርጅቶች የመገንጠል ዓላማ ያላቸውን ኃይሎች ኢትዮጵያዊነትን እንዲቀበሉና የፖለቲካ መሸጋሸግ እንዲፈጠር ከማበረታታት ይልቅ በነፃነትና በዴሞክራሲ ጭንብል ግንጠላን ሊሸፋፍኑ መሞከር አይጠበቅባቸውም የምንለው። ጠባብ ብሄረተኞቹ በግልጥ የአቋም ለውጥ ካደረጉ ግን  ሊቀበሏቸውና በሀገራዊ የትግል ማዕቀፉ ውስጥ ሊያስገቧቸው ይገባል። ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት “ጠባብ አመለካከታቸውን ትተዋል” እየተባለ ሊነገረን የሚሞከረው ከእውነት የራቀ ነው። እንደ ድርጅት በጉባዔ ውሳኔ “ዓላማችን በአንድነት መኖር ነው አላሉም”፤ እንደ ድርጅት “ኢትዮጵያውያን ነን” የሚል አቋም አልወሰዱም።

እነዚህ ፀረ-አንድነት ኃይሎች እንወክለዋለን ከሚሉት ብሄር/ብሄረስብ ውስጥ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት መስዋዕትነትን እንዳልከፈሉና አሁንም በኢትዮጵያዊነታቸው እንዳልቆሙ ሁሉ፣ በጣት የሚቆጠሩ የብሄረሰቦቹ ተወላጆች በሰሜን አሜሪካ እንደአመቺነቱ በተወሰኑ ስብሰባዎች ላይ አንድነትን አመላካች የሆኑ ነገሮችን ተናገሩ በሚል የፀረ-አንድነት ኃይሎች አቋሞች እንደተቀየሩ ተደርጎ መለፈፉ

እውነታውንና ያለውን ሁኔታ የሚያንጸባርቅ አይደለም። በአንድ ሀገር ውስጥ፣ የዜጎች እኩልነት ተረጋግጦ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተመሥርቶ የሁሉም ባህልና ቋንቋ ተከብሮ...ወዘተ ወደፊት አብሮ ለመኖር ዝግጁ መሆናቸውን እንደድርጅት ራሳቸው እስከዛሬ አልነገሩንም። እንዲያውም አሁንም በድረ-ገፃቸው ላይ ሰፍሮ ያለው አቋማቸው ኢትዮጵያን በወራሪነትና በቅኝ ገዥነት የሚከስና ፀረ-አንድነት መሆናቸውን ግልጥ አድርጎ የሚያሳይ ነው።

እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ በአንድ በኩል ሥልጣን ላይ ያለው ቡድን በሕዝባዊ ይሁንታ ሳይሆን በነፍጥ አስገድዶ የሚገዛውን ሕዝብ በሚናገረው ቋንቋ መሠረት ከፋፍሎና አለያይቶ፣ ከአንድነቱ ይልቅ ልዩነቱን እያጎላ የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም ሲጥር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጭቆናን፣ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ነፈጋን፣ ግፍና ዕመቃን በመቃወም ለመብት መከበር ገገርውን ቡድን የሚታገሉ በርካታ በተቃዋሚነት የተሠለፉ የብሄር ድርጅቶች ከአንድነት ኃይሉ ጎን ተስልፈው ሲቆሙ፤ ከዚህ ተጻረው ደግሞ ፀረ-አንድነት ሃይሎች የጭቆናውና የግፉ ምንጭ ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያ እንደሆነች አድርገው ከራሱ ከገገርው ቡድን ባልተናነሰ፣ አንዳንዴም በከፋ ሁኔታ፣ የዘር ጥላቻን በማናፈስና በመቀፍቀፍ የቆየ የመገንጠል ዓላማቸውን ዕውን ለማድረግ ምቹ ሁኔታን በመጠባበቅ ላይ ነው የሚገኙት። ይህ ሀቅ በመሆኑ፤ አንዳንዶች ሊያዘናጉን እንደሚሞክሩት፤ በሀገር አንድነት ላይ የተቃጣውን አደጋ አቃለንና አሳንሰን በፍጹም ልናየው አይቻለንም። ዛሬም እንደትናንቱ በአንደበታቸውም ሆነ በጽሁፋቸው ኢትዮጵያን እንደ ወራሪና ቅኝ ገዢ የሚያዩና ሕዝቧንም እንደ ጠላት የሚፈርጁ ቡድኖች በተቃዋሚው ፖለቲካ ምህዋር ውስጥ ቦታ አግኝተው እስካሉና ለዚህም ግባቸው እስከተንቀደሰቀሱ ድረስ፣ ሀገርን የማፍረስ ግባቸው ተግባራዊ እንዳይሆን መከላከል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሄራዊ ግዴታ ነው እንላለን።

በተለይም ደግሞ፣ በፀረ-አንድነት ኃይሎች ስብስብና ጡንቻ ኤርትራን በመገንጠልና በማስገንጠል የፈጠሩት አደጋ ተጠቂ የሆነችው ሀገራችን፣ ቀጣይ ለሆነ ሌላ አደጋ እንድትጋለጥ ተቀምጣችሁ ተመልከቱ መባሉ የሚያሳየው ቢያንስ የሚቀርበው ሀሳብ በጥሞና ያልተጤነ መሆኑንና ከዚህም ከቅርብ ጊዜ የሀገራችን ታሪክ እንኳ ለመማር ፈቃደኝነቱ እንደሌለን ነው። በዚህም ምክንያት ከቱኒዚያና ከግብጽ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለመማር ከመነሳት በፊት፣ ከሀገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ መማራችን ይቅደም እንድንል እንገደዳለን። የራሱን ታሪክ ለዘነጋ ወገን፤ በተለይም የዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ የተፈጸመውን፤ ያንኑ ዓይነት አሳፋሪ ታሪክ ዛሬም እንዳይደግመው ረጋ በል፣ አስበህ ተራመድ ልንለው ይገባናል።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በቅድሚያ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች በመሠረታዊ ሀገራዊ ዓላማዎች ላይ ተስማምተው ዛሬ የመለስን አምባገነናዊ አገዛዝ በጋራ ለማስወገድ መተባበር አለባቸው ብሎ ያምናል። እነዚህ ዴሞክራሲያዊ የአንድነት ኃይሎች የትግል ግባቸው የመለስን መንግሥት ማሰወገድ ብቻ ሳይሆን በምትኩም በዜጎች እኩልነት ላይ የተመሠረተች ፍትሃዊትና ዴሞክራሲያዊት የሆነች

አንዲት ኢትዮጵያን መገንባት መሆኑ በግልጥ እንደ ዓላማ ሊቀመጥ ይገባል ብሎ ድርጅታችን ያምናል። ለዚህ ግብም ከማንኛውም ይህን ዕምነት ከሚጋራ ፖለቲካዊ ድርጅትም ይሁን ማኅበራዊ ተቋም ጋር በመተባበር ለመሥራት ዝግጁ ነው፤ በዚህ ዙሪያ ያላሰለስ ጥረትም ያደርጋል። ዓላማቸው ሀገራችንን መገንጠል ከሆኑ ቡድኖች ጋር ይህን የመገንጠል ዓላማቸውን ዕውን ለማድረግ እስከታገሉ ድረስ፤ ተባብረን መሥራት አይደለም፤ ፀረ-አንድነት ዓላማቸው ራሱ እንዳይሠምር አጥብቀን እንታገላቸዋለን።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በሥልጣን ላይ ያለውን አምባገነንና ጎጠኛ ቡድን አሸቀንጥረው ለመጣል ኢትዮጵያውያን በሚመስላቸው መልክ መደራጀትና መታገል አለባቸው ብሎ ያምናል። በተለያየ መልክ ቢደራጁም እንኳን የጋራችን በሆነው በኢትዮጵያ ህልውና ጉዳይና የዴሞክራሲ ጥያቄ ዙሪያ መተባበርና ትግላቸውን ማስተባበርም አለባቸው እንላለን።

የቅርብ ጊዜውን የግብጽንና የቱኒዚያን ሕዝባዊ ዕምቢተኛነት "ተሞክሮ" በተሳሳተ መልክ በመተርጎም የመደራጀትና የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ አንድነት የመምጣታቸውን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ዝቅ ለማድረግ የሚደረገው ሙከራም አዘናጊና የተሳሳተ ፖለቲካዊ ዝንባሌ እንደሆነ እናያለን። ያልተደራጀ ሕዝብ አያሸንፍም! አያሸንፍም ስንል አንድን መንግሥት ግብታዊ በሆነና ባልተደራጀ መልክ መጣል በፍጹም አይቻልም ከሚል ዕምነት በመነሳት ግን አይደለም። ግብታዊ የሕዝብ መነሳሳት መንግሥትን መጣል እንደሚችል ለመረዳት ወደ ቱኒዚያና ወደ ግብፅ ከመሄድ ወደ ሀገራችን ታሪክ መለስ ብለን ብንመረምር የምናጣው አይደለም። ነገር ግን፣ ሕዝብ ከሚያልመው ግብ ለመድረስና በመስዋዕትነት የሚያገኛቸውን ድሎች ሊነጥቁት የሚመጡትን ቀማኞች ሁሉ በስልት ለመከላከል ደግሞ መደራጅት የግድ የሚያስፈልግ ነው። የስድሣ ስድስቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት መጣል ቢችልም እንኳን አበባ ፈክቶ ፍሬውም አሽቶ ጎምርቶ እያለ ሞጭልፎ የወሰደው በወቅቱ ተደራጅቶ የነበረው ወታደራዊ ኃይል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ሕዝብ የድሉ ባለቤት ሊሆን አልቻለም። እንዲያውም ዘውዳዊውን መንግሥት ተክቶ ሥልጣን የያዘው ወታደራዊ ደርግ ቀድሞት ከነበረው የአፄያዊ ሥርዓት የከፋና የከረፋ አምባገነን ሆኖና አንድን ትውልድ መትሮ ሲያበቃ፤ እነሆ ዛሬ ደግሞ ከሱም ለከፋና ሕዝብን ብቻ ሳይሆን አገርንም ለሚመትር ሌላ አምባገነን ሥርዓት ዳርጎን ነው ያለፈው። የግብፁንም ዕውነታ ስንመለከት ሥልጣኑን የተረከቡት ሕዝባዊ እምቢተኞቹ/አመጹን የመሩት ወገኖች ሳይሆኑ የተደራጀውና እስካፍንጫው የታጠቀው ወገን ነው። ከኢትዮጵያው ሁኔታ ለየት ቢልም እንኳን የራሱ የሙባረክ የወታደሩ ክፍል ስለሆነ፤ ይህም ቢሆን የሚያሳስብ እንጂ የሚያበረታታ አይደለም። ገና በሕዝቡ ድልና የሥልጣን ባለቤትነት ያልተጠናቀቀ የለውጥ ሂደትንና ጉዞውን ነው የምናየው። ከዚህም አልፎ ተርፎ ቀድመው ተደራጅተው የቆዩትና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ፓርቲዎች፣ ሕዝብ የታገለለትን የፍትህና የዴሞክራሲ መብት ጥያቄ በቀላሉ መፈታተን የጀመሩበት ሁኔታ እየተከሰተ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው የዴሞክራሲ ኃይሎች ቀድመው የሽግግር ሂደቱን ሊረከቡ የሚያስችላቸው የተደራጀ አማራጭ የፖለቲካ ኃይል ባለማዘጋጀታቸው ነው።

ስለዚህ የግብፅም ሆነ የቱኒዚያ ተመክሮ የመደራጀትን ጠቀሜታ ወደጎን ለመግፋት፣ ለማቃለልና አስፈላጊነቱንም ለማጣጣል የሚያስችል ግንዛቤን ሊያስገበየን የሚያስችል ክህሎት የለውም። ግብታዊና ያልተደራጀ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ ማጋነን ደግሞ ኢትዮጵያን ሊጠቅም አይችልም። ተደራጅተውና፣ አነሰም በዛ፣ መሣሪያ ታጥቀው በኢሳይያስ አስተባባሪነት ወዲያና ወዲህ ለሚሉት ፀረ-አንድነት ኃይሎች የመስረጊያ ክፍተትን በመፍጠር ሀገርንና ሕዝብን ከአንድ አደጋ ወደ ሌላ፣ ምናልባትም ወደ ከፋም ሊሆን ወደሚችል፣ ማሸጋገር ነው የሚሆነው። ይህ አካሄድ የሕዝብን የበላይነት ዕውን ያደረገ በአንድነት ላይ የሚመሠረት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በአስተማማኝ መልክ ለማምጣት ቀርቶ ለቀጣይ አምባገነናዊ ሥርዓት፣ ለከፋ ሀገራዊ መናጋት፣ ለተራዘመ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ቀውስም እንዳይዳርገን ያሠጋል።

በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በግብፅና በቱኒዚያ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በማነጻጸር፣ ያሉትን ልዩነቶችና እነዚህም በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልና መነሳሳት ላይ የሚኖራቸውን የተለየ ጫና ማጤን ያሻል። ለምሳሌ ሁሉም ግብፃውያን ለውጥ እንዲመጣ ሲጠይቁ የሀገራቸውን ኅልውናና አንድነት በጥያቄ ውስጥ አላስገቡም፣ የነገና የተነገወዲያ ጉዳይም አላደረጉትም። ጥያቄያቸው የመንግሥትና የሥርዓት ለውጥ ስለማምጣት ነበር። በቱኒዚያም ውስጥ እንደዚያው ነበር የሆነው። አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ከዚህ የተለየ ነው። ሀገራዊ ስሜታቸው የተመናመነ፣ በዘውግ ስሜት የነበዙ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ የጦርና የፖሊስ ኃይል አዛዦችና መኮንኖች የሚያዙት የጦርና የፖሊስ ኃይልና ሌሎችም የፀጥታ ኃይሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲነሳሳ እንደ ግብፁ ጦር ሳይሆን እንደ ሊቢያው ቃዳፊ፤ እንደ የመኑ ሣሊህና እንደሶሪያው አልአሳድ የጦር ኃይሎች ሕዝብን ከመጨፍጨፍ ወደኋላ የማይሉ በመሆናቸው (ምርጫ 97ትን ያስታወሷል) ማንም ቡድን የአንድነት ኃይሎችን ሊያዘናጋ አይገባም እንላለን። ይህን መካድ ከጥፋት አልፎ በሕዝብ ላይ የሚቃጣ ትልቅ በደልም ይሆናል! የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊነትና ጨካኝነት ከተጠቀሱት መሰሎቹ፣ ከቃዳፊ፤ ከሣሊህና ከአልአሳድ የሚያንስ እንዳልሆነ ኢትዮጵያውያን ያውቃሉና!

የግብፅንና የቱኒዚያን ሕዝባዊ መነሳሳት ስናነሳ አንደኛ እነዚህ መነሳሳቶች ገና በሕዝቡ ዘላቂ ድል አለመጠናቀቃቸውን መገንዘብና ጎን ለጎን ደግሞ እስካሁን ያልተሳኩ ሌሎችን ሕዝባዊ መነሳሳቶችንም በመቃኘት ትምህርት ልንወስድ ይገባል። ከገዥዎቹ ባህሪያት ስንነሳ ከኢትዮጵያው ጋር ይበልጥ ተቀራራቢነት ሊኖረው የሚችለውን አሁን በሊቢያ፤ በየመን፤ በባህሬንና በሶሪያ ያሉትን ሁኔታዎችንም መመርመር ያስፈልጋል። ከሀገራችን ሁኔታ ጋር ያለውን ተዛምዶና ልዩነት በቅርብ መረዳትና ማገናዘብም የግድ ነው። በተወሰነ ደረጃ የተሳካውን “የጣህሪር አደባባይ” ሕዝባዊ መነሳሳት ስናነሳ የዴሞክራሲ ኃይሎችንና ንቅናቄያቸውን ያኮላሸውን የቻይናውን የቲያንማን አደባባይን ታሪክ መዳሰስ አለበት። የግብጽና የቱኒዚያን ሠራዊት ከሕዝብ ጋር መቆምን ስናስብ፣ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ሥር የሆነውን የቻይናን ቀይ ሠራዊት ድርጊትና ውጤቱን ማገናዘብና እንዲህ ዓይነቱ ችግር ቢገጥም ለዚህ ምላሽ የሚሰጥ መላ ከወዲሁ መፍጠር ይጠበቅብናል። ይህን ሁሉ ደምሮና

ቀንሶ ውጤቱ ሲታይ፣ ይህ የምናደርገው ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል የሚጠይቀው ሰከን ማለትን፣ ተባብሮ በአንድነት መቆምን፣ በሀገራችን ምድር በስፋት መደራጀትንና ሕዝብ ትግሉን በሚመሩት ኃይሎች ላይ ዕምነት እንዲኖረውና ተተውት እንደማያፈገፍጉ፣ እስከ መጨረሻው ከጎኑ እንደማይለዩ ማረጋገጥን ነው እንጂ፤ የግብር ይውጣና ሃላፊነት የጎደለው ሥራን አይደለም። አንዳንዶቹ "መደራጀትና ማደራጀት ይቅደሙ፣ በበቂ ያልተደራጀን ሕዝብ ከሩቅ ሆኖ ተነስ ማለት ቢያንስ ለዚያ ሕዝብ ስቃይና እልቂት ደንታ-ቢስ መሆን ነው" የምንለውን ወገኖች "እኛ ዝግጁ እስከምንሆን የመለስን መንግሥት አትነካኩት" ይላሉ ይሉናል። የምንለውን አዛቡብን እንጂ የምንለው ነገር ግን አለን። እኛ የምንለውማ "እናንተም በበቂ ተዘጋጁ ግልጽና ዘላቂ ሀገራዊ ዓላማም ያዙ ነው የምንለው!!"። የሀገራችን ሁኔታ ስለሚመለከተን ተገቢ የሚመስለንን ደግሞ ዛሬም ሆነ ነገ ደፈር ብለን እንናገራለን። እንኳን የአንድ ሀገርን ሁኔታ ስለመለወጥ የሚሠራ እንቅስቃሴ፣ ለበዓል መዋያ እንጀራ አስፈልጎት ሊጥን የሚያቦካ ሰው፣ ጋግሮ መብላትና ማብላትም እንዳለበት ሊያውቅ ይገባልና!

የጋራ የሆነችውን ሀገራችን ለማዳን ዛሬም ትክክለኛው መንገድ ሁሉም የአንድነት ኃይሎች በሕዝቡ እኩልነት ላይ ለተመሠረተ ሀገራዊ አንድነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለፍትኅ፣ ለሕግ የበላይነት፣ በአንድነት ለመታገል መቻላቸው ነው እንላለን። የጋራ ዓላማዎቻችንን ለመሳካት ከኢ.ሕ.አ.ፓ (ዴሞክራሲዊ)ና አብረው እየሠሩ ካሉት የአንድነት ኃይሎች ጋር ተባብረን እንሥራ በማለት አሁንም ጥሪያችንን በድጋሚ እናቀርባለን።

በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነቷን የጠበቀች ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ትግል ትመሠረታለች!!